ይሉኝታ ቢሱ ወያኔ በሚኒሶታ ቅሌቱን ተከናነበ።

ሰኔ 22 ቀን 2014 ዓ.ም በአላሙዲ የሚደገፈው የወያኔ ቡድን የሚኒሶታን ሕዝብና ሌላውን ኢትዮጵያዊ ለማደናገር በሚኒሶታ ጠቅላይ ግዛት በሴይንት ፓውል ከተማ በሚገኘው ኮንኮርዲያ ዩኒቨርሲት እስፖርት ሜዳ ላይ ባዶ እስታድየሙን በመያዝ ቅሌቱን ተከናንቧል። ሕዝብን በመፍረት የስታድየሙን ዙሪያ በአረንጓዴ፣ ብጫ ፣ ቀይ ባንድራ ሰቅለው ነበር። ለተቃውሞ የወጣውም ሕዝብ በአገር ቤትና በወያኔ ቤተክርስቲያኖች የሚጠቀሙበትን ወያኔ በባንድራችን ላይ የለጠፈውን የሴይጣን ምልክት ያለበትን ባንድራ አለመጠቀማቸውን በማየት በኢትዮጵያ ባንድራ መቀለድ አይቻልም፤ በባንድራ ማታለል አትችሉም። ወያኔ ይህ ባንድራ አያውቅም፣ ይህን የኢትዮጵያን ባንድራ(አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀይ ቀለማት ብቻ ያለበትን ሳንደቅዓላማ) ለሁሌም ተጠቀሙ በማለት ተቃውሞና ማሳሳቢያ ሰጥቷል። በመኪና ማቆሚያ ከዚያም በሸቦ አጥር እንዲሁም በለመዱበት የፍራቻቸው መከለከያ በሆነው ፖሊስ በውጭና በውስጥ የተከበበውና የተጀበው የኮንኮርዲያ ዩንቨርሲቲ ስታድየም ወያኔዎች ይበልጥ ከሕዝብ ወለፈን እንዲርቁ ረድቷል።

ወያኔ በኢትዮጵያውያን ስፖርት ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ ላይ ያደረገውን የከፍፍልና በስፖርት ስም በሚኒሶታ ለማካሔድ ያሰባውን ድርጊት የሚቃወመው ሕዝብ የወያኔና የአላሙዲ ገንዘብ ተቀባዮች ወደሚጫወቱበት ሜዳ ድረስ በመሄድ ተቃውሙን በመፈክር ፣ በዘማሬና በጩሃት አሳምቷል። በወቅቱ ሕዝቡ ካሰማቸውና ከያዛቸው መፈክሮች ጥቂቶቹ ፡-

- ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!
- Long Live Ethiopia !!!
- ዘረኝነት ይቁም !
- Stop Tribalism!
- Free Tsegaye Debteraw
- Free Eskender Nega
- Free Andoalem Arage
- Free Rhiot Alemu
- Free Aberash Berta
- Free all political prisoners in Ethiopia
- Stop Killing Ethiopians
- Stop Arresting Journalists
- Stop Genocide in Ethiopia
- We oppose recent killings of Oromo students in Ethiopia
- Stop selling Ethiopia' s land for Arabs and others
- ሕዝብ ማፈናቀሉ ይቁም
- በደም ገንዘብ ስፖርት ማካሄድ አይቻልም
- በእስፖርት ስም የኢትዮጵያ ሕዝብ አይታለልም
- ሚኒሶታ ለሕዝብ ጠላት መሸሸጊያ አትሆንም
- አንድ ነን አንከፋፈልም
- የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል
- በባዶ ስታደየም ጫወታ የለም። ወያኔን ሕዝብ እንደማይወደው ከዚህ ተማሩ
- እናንት ተጫዋቾች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰለፉ
- የደም ገንዘብ ይቅርባችሁ

ከመዝሙሮቹ ውስጥ፡-

- *አትነሰም ወይ አትነሰም ወይ ይሕ ባንድራ ያንተ ኣይደለም ወይ*
- *እናት ኢትዮጵያ* ***የደፈረሽ ይውደም*** *የደፈረሽ ይውደም*

ሰልፈኛው በ4፡30 ፕም ላይ በሱተር ታርጌት ተሰብስቦ ወደፊት እቅድ ወጥቶ ተከታታይ ሰልፎች እንዲካሄዱ ወሰኖ የሚኒሶታ ህዝብ የወያኔን ሲታድየም ባዶ በማደረጉ ምስጋና አቅርቧል። በስብሰባው የተገኘው ሰልፈኛ በሚኒሶታ የሚገኙት ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ከእነዚህ የወያኔ ከፋፈይ ቡድኖች ጋር በማንኛውም ጉዳይ ትብብር እንዳይደርግ በአክብሮትና በወያኔ እየተበደለ ባለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ጠይቋል። ዘረኞቹ መገለል ይኖርባቸዋል።ወደፊት በሚካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎች የሚኒሶታ ሕዝብ እንዲገኝ በሚኒሶታ የተቋቋመው ግብረ ኃይል ጥሪውን በድጋሚ ያቀርባል።

በሚኒሶታ የተቋቋመው ግብረኃይል